አሰባሳቢ ማንነት ባንድ አገር ልጅነት
የኢትዮጵያ እጣ ፋንታ
ጸሐፊው ዩሱፍ ያሲን ወይም የትላንቱ የጦቢያው መጽሔት ብዕረኛ ሐሰን ዑመር ዓብደላ
ቅኝት- ዘኢትዮጵያ ጋዜጣ

በገዢው ፓርቲ በመንግሥትም ይሁን በተቃዋሚው ጎራ ያሉ ፖለቲከኞች፣ በነጻነት ስም የሚያስሩትም የሚገድሉትም፣ ከመድረኩ የሚቆሙትም፣ ከአዳራሹ ተገኝተው የሚያጨብጭቡትም ፣ በየድህረ ገጹ የሚጽፉትም፣ ብሔሬን፣ ሃይማኖቴን፣ መንግሥቴን፣ ንግግሬን፣ ነጻነቴን... የሚሉትና ተነጣጥለው የተጠነለ አጀንዳ ይዘው የሚኳትኑት ሁሉ ምን እያሉ ምን እያደረጉ እንደሆነ ቆም ብለው እንዲያስተውሉ ማድረግ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ይህን መጽሐፍ ማስነበብ ነበር። ግን ከጥቂቶች በቀር ምናልባት ብዙዎች እንዳሻቸው በሚያናግራቸው የእርግጠኝነት እውቀት ተሞልተዋልና በዚያ ላይ ንባብ አለመውደዱም ታክሎበት፣ አእምሮ የተጨመቀበት፣ ታሪክ ለታሪክ የተሟገተበት፣ እንዲህ ያለ መጽሐፍ ዝምብሎ ይቀር ይሆን እንዴ ማሰባሉ አይቀርም።
እንዲህ ሆነ፣ እንዲህ ተደረገ የሚል ሰውና ድርጅት ላይ የተንጠለጠለ፣ አንዱን አንስቶ አንዱን የገደለ መጽሐፍ አይደለም። ልክ ነኝ ወይም ልክ ነበርን፣ ትግላችን፣ ገድላችን፣ መስዋዕትነታችን የሚል፣ ራስን እያሞገሰ ወንድምን እየከሰሰ የተኮፈሰ መጽሐፍ አይደለም። የኔ ወገን ተረገጠ፣ ተደፈጠጠ፣ ያኛው ረገጠ - ይሄ ተረገጠ፣ እያለ ወቃሽ፣ ነቃሽ፣ ቀስቃሽ፣ አስለቃሽ መጽሐፍ አይደለም። ኢትዮጵያውያንን ሁሉ አቅፎ የተመለከተ፣ ተቃቅፈውም እንዲተያዩ የጋበዘ፣ አእምሮን እያፍታታ ወደ ለውጥ የሚጣራ ቅን መጽሐፍ ነው።

ወደየትም አቅጣጫ ከሚለጠጥ የኢትዮጵያ ታሪክ ጫፍ ይዞ ጥራዝ ነጥቆ የሚሮጥ መጽሐፍ አይደለም። ከአገር ብቻ ሳይሆን ከሀሳብም ጭምር ፍቅር የወደቀ ሰው በየገጹ ቀና ማለቱ አይቀርም። እናም ቆም ብለን ማሰብ ይኖርብናል ፤ ማሰብ ማሰላሰል፣ የችግራችንን መሠረት መፈተሽ፣ ከዚያም የተቀዳ መፍትሄን መሻት ያስፈልገናል የሚሉ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ “አስገድዶ’ ማስነበብ የሚቻል ቢሆን ይህንንም መጽሐፍ እንዲያነቡ ማስገደድ በተቻለ ነበር። ግን መጽሐፉ ራሱ ከነገረ ሥራው ሁሉ “ማስገደድን” ይቃወማል። ነገሮችን ሁሉ ለምርጫ አለመተውን የችግሮቻችን ሁሉ ቁንጮ አድርጎ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። እንዲያውም ርቆ ሄዶ ሕገመንግሥቱ ውስጥ ራሱ ይሄ “የህዝበ ውሳኔ” (ሪፈረንደም) ነገር መካተት አለበት ባይ ነው። “ከመንግሥት አደረጃጀት በተጨማሪ ውሳኔ ሕዝብ ሊጠይቅባቸው የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች” መኖራቸውን ጽፏል። “በአሁኑ ሕግ መንግሥት ሪፈረንደም የሚባል የመራጩ ሕዝብ ፍላጎት ማወቂያ ሥነ-አወሳሰን የሚባል ነገር አልተወሳም።” ብሏል። ፖለቲካችን ገና ከአናቱ ሕገመንግሥትና የህዝብ ድምጽ ያልተገናኙበት፣ አስፈላጊነቱም ሆነ ቅድሚያነቱም

ትኩረት ያላገኘበት ጉዳይ መሆኑን መጽሐፉ ያሳስባል። እንዲያውም ድምጽ ከመስጠታችንም በፊትስ ቢሆን ሕገመንግሥታችን ማን እንደሆነ የት ያውቀናል? ማንነታችንን አስማምቶም አብራርቶም ሳይገልጽ እንዴት አድርጎ ባንድ አገር ልጅነት ያሰባስበናል? የሚል ጥያቄም ያጭራል። ማንነትና ፖለቲካው የመጽሐፉ አንኳር ፍሬ ነገር ነው። ጸሐፊው በመቅድማቸው ላይ የሚከተለውን ብለዋል፡-

በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ አንገብጋቢና ወሳኝ ሀገራዊ ርእሰ ጉዳይ መምረጡ እምብዛም ጊዜ አልፈጀብኝም። ለሃገሪቷ ባለድርሻ ስብስቦች ቀጣይ አብሮነት ብቻ ሳይሆን ዛሬ ለሕልውናዋም ጭምር ተፈታታኝ ተግዳሮት የጋረጠው ጉዳይ እምብዛም አላመራመረኝም። የማንነት ፖለቲካና ተግባራዊ እንደምታዎች ናቸው ወደሚለው ውሳኔ ደረስኩና የመጽሐፉ ማጠንጠኛ ይህው አብዛኛው ይህንኑ ባለብዙ ፈርጅና ደርዝ ያለው ማንነት የተሰኘ ፅንሰ-ሐሳብ በየሚያፍታቱና በሚበልቱ ምዕራፎች ተዋቀረ።”

መጽሐፍ ስለመጽሐፉ እንደሚለው፣ “ከስሙ ጀምሮ እስከ ማለቂያው ድረስ የመጽሐፉ ማጠንጠኛው ማንነትና በዚህ ወገንተኛነት በሚፈጠሩ የሰው ልጆች ስብስቦች መቧደንን መነሻ ያደረገ ነው። በመካከላቸው የሚፈጠር አለመግባባትን ወይም ውዝግብን ይቃኛል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ዓላማውና መዳረሻው ያደረገውን “አሰባሳቢ ማንነት ባንድ ሃገር ልጅነት " መሠረት ያደረገ የብሔረሰቦች የአብሮነት ቀመር ለማፈላለግና ለማግኘት ነው። ስለዚህ የግድ ማንነት በተሰኘው ፅንሰ-ሓሐሳብ መጀመር እንደነበረበት ይገልጻል። “ማንነት” ሲባል ባጭሩ “አንድ ስብስብ እሱን ከሌሎቹ ስብስቦች የሚለዩትን መታወቂያ መለያዎቼ ናቸው በሚላቸው ተጋሪዮሾቹ (COMMONNESS) ላይ ተመርኩዞ ወገንተኛነት የመፍጠር ክንዋኔ ነው።” (ገጽ 7)

“በሃገራችን ትክክለኛው ትርጉሞቻቸው በቅጡና በተገቢ መንገድ ባልተብራራው ብሄር፤ ብሔረሰብና ሕዝብ እንደ ማህበረሰብ ስብስቦች የእድገት ደረጃዎች መመዘኛ ተደርገው ብዙ የተነገረበት፤ ብዙ መፃሕፍት በተፃፉበት እንዲያውም ተደጋግሞ እንደተነገረው የብሔር ጉዳይና መፍትሔዎች የኢትዮጵያ ተማሪ ንቅናቄ የፖለቲካ አፍ መፍቻ ነበር ።” እያለ “በቅርቡ በዓለም ላይ ብዙ እየተባለለት የመጣው ኤትኒክ ጉሩፕና ግሩፕና ኤትኒስቲ የተሰኙት ንባቤ-ቃሎች ያላቸው ተዛማጅነት፤” እያስተያየ ይተቻል። (ገጽ 68-69) ዞሮ ዞሮ ሁሉም ስለማንነት ነው። ወይ ስለሚያኮራው ወይም የሐፍረትና የስጋት ምንጭ ስለሆነው ማንነት?

ኩራት፣ ኩራት አይላችሁም ወይ!
ይህ ሁሉ ታሪክ የኛ አይደለም ወይ!

ስጋት ፣ ስጋት አይላችሁም ወይ!
የከበበን ሁላ ጠላት አይደለም ወይ! 73

በኩራት ተዘናግታ የምታብጥ፣ በስጋት የምትናጥ፣ ከወደፊቱ ቀርታ ወደ ኋላ ተንጠራርታ፣ ሲርባት ታሪክ ጠርታ ኩራት በልታ ስለ ነገ ተስፋዋ ሰግታ የምታድር አገር መሆናዋን ለማሳየት የሞከረ መጽሐፍ ነው ። ስለሆነም በምን ፤ በምን እንኮራለን? ከምን፤ ከምንስ እንሰጋለን? እያለ ይጠይቃል።

በምን መኩራራት እንዳለብንም ሆነ ከምን መስጋት እንዳለብን በቅጡ ፈትሾ መረዳትን የመሰለ ቁም ነገር የለም። ለተግባራዊ መከላከያ እርምጃ ሊያዘጋጀን የሚችለውም ይህ ዓይነቱ እውቀት ነው። የኩራት ምንጮቻችን ምን ምን መሆን እንደሚችሉ በወጉና በቅጡ ንቅስ ተደርገው መለየት አለባቸው። የስጋት ምንጮቻችንም እንዲሁ። የኩራት ምንጮቻችን በጊዜው የሚቀያየሩ አይደሉም። የስጋቱ ሥዕል ግን ወደኋላ ላይ እንደምንመለከተው ተለዋዋጭ ነው። በየጊዜው መልኩ የሚቀያየር። እንደ መጽሐፉ አባባል ኩራት ቋሚ ሲሆን ስጋት ግን ተቀያያሪ ነው። የምንኮራበት ያው ሆኖ በየጊዜው የሚያሰጋን ነገር ግን ይቀያየራል። ባለፈው የቅድመ አያቶቻችን ታሪክ ከመኩራራቱ እኩል ያለንበትን አንገት አስደፊ ሁኔታ በምር መፈተሹ ጤነኛ አካሄድ ነው። ምን ነካን ብሎ መቆዘሙ የመፍትሔ ፍለጋው ጅማሮ ነውና። ፈረንጆቹ Soul searching የሚሉት መሆኑ ነው። በስሜቶች ከመብሰክሰክ የዘለለ የራስ ፍተሻ ክንዋኔ ነው።

ከሁሉ በፊት ግን ያለ ምንም ውዳሴ ራሱ ኋላ ቀርነታችንን ከተቀበልንና ምክንያቶችን በግልፅ የመነጋገር ድፍረት ከታከለበት መፍትሔ ማግኘቱ አዳጋች ሊሆን አይችልም። ምክንያቶቹን ፍለጋ መኳተኑ ቀጣዩ እርምጃችን ነው የሚሆነው። .... ምስጢሩን ፈልጎ መፍትሔ መጠቆሙ ደግሞ የተቀነባበረ የምርምርና የጥናት ውጤት ነው መሆን የሚችለው። መጽሐፉ ይህን "ለምን ወደኋላ ቀረን? ለምንስ ሌሎቹ ጥለውን ሄዱ?" በተሰኘው ምዕራፉ ለኋላ ቀርነታችን ምክንያቶች በሚገባ ዘርዝሮ ለማስቀመጥ ሞክሯል። ስለኩራታችን ምክንያት ሲያብራራ የሚከተለውን ጽፏል፡-

ያለ ጥርጥር፣ ከልብ ከምንኮራበት አንዱ የቀደምት ባለታሪክ ሕዝቦች አባልነታችን ነው። ሜሶፖታሚያ፤ ግብፅ፣ ግሪክ፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ኢራንን የመሳሰሉ ቀደምት ሥልጣኔዎችና መንግሥታት ታሪክ ተጋሪነትና የዕድሜ አቻነት ነው። ከቅርቡ የመንግሥታት የታሪክ መዛግብት የገቡትን እነ አሜሪካንን የማይጨምር ይህ ተርታ ነው። ይህንን አፅንኦት ለመስጠት ይመስላል ዘፋኙ እንዲህ  ይላል፤

ሃበሻ አገር ኖሮት- በታሪክ ላይ ሲጣፍ
አውሮጳ ያን ጊዜ- አልወረደም ከዛፍ
ካሌብ ምድረ-አረብን- አፍሪካን ሲያስገብር
የአሜሪካ ምድር- አልተገኘም ነበር

እኛ ኢትዮጵያውያን የቀደምት ባለታሪክ ሃገር መሆናችንን ለማመልከት ነው። እነሱ ከዛፍ ሳይወርዱ እኛ ይህንን እናደርግ ነበረ ነው የኩራት ምንጬ። ቀደምትነታችንን ለማስረገጥ። ታዲያ አሁን ምን ነካችሁ? ብንባልስ መልሳችን ምንድነው? ቀዳማውያኑ ደሐራውያን ይሆናሉ ብሏል መፅሐፉ ብለን በግዕዝ መመለሱ የብዙዎቹ ታሪክ አጥኚዎቹ ተመራማሪ ፈታሽነት አያጠግብም። ጉዳዩ ግን አሁን ለምን ወደኋላ ቀራችሁ ብቻም አይደለም። እነዚያ ሃገሮች ማለት ሞሶፖታሚያ፣ ቻይና፣ ግብፅ፣ ሮም፣ ህንድና ኢራን የታሪካቸውን ገናናነት በሰነድ መልክ እንደሚያስቀምጡት እኛ ይህንን ማስመስከር አለመቻላችን ጉዳይ ነው። በቅርፃ ቅርጽነቱ፣ ለትውልድ ለማስተላለፍ በሚችሉበት በፅሑፍ ሙዳይነት አልተቀመጠልንም። አንድ ወዳጄ ስመጥር የሆነው የቀድሞ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የጸጥታ አማካሪና እስተራተጂስት ሄንሪ ኪሲንጀር የኢትዮጵያ የሥልጣኔ ታሪክ ምናልባት ከቻይና ሥልጣኔ ሊቀድም ይችላል ሲል በጆሮው ማዳመጡን አረጋግጦልኛል። ተደጋግሞ ከሚወሳው 3000 ዓመት የመንግሥትነት ታሪክ በተጨማሪ አንዳንድ የታሪክ ምሁራኖቻችን ወደኋላ በመለጠጥ ወደ 6000 ያደርጉታል።

መዋረዱን ተረድቶ ምክንያቶችን በመፈተሽ መፍትሔ ሓሐሳቦችን ማቅረቡ ነው ቁም ነገሩ። ቁም ነገሩ አለመውደቅ ሳይሆን ወድቆ መነሳቱ መቻሉ ላይ ነው ተብሏልና። አዲሱም አዎንታዊው ተነሳሽነቱም እሱ ነው። "የስጋቱ ምንጭ ከታወቀ መፍትሔው አያስቸግርምና። "90

ለብሔራዊ ማንነታችን መብላላትና ነጥሮ መውጣትም የማይናቅ ድርሻ ያበረክታሉ። የስጋቶቻችንን ምንጮች ማወቁም የደህንነታችንን ማስጠበቂያ መሰናዶዎች ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ይህም በተራው የሕልውናችን አስተማማኝ ማረጋገጫ ዋስትና መሆኑ እሙን ነው። የስጋታችን ምንጮች አንድ ባንድ፤ የኩራታችን ምንጮችም እንዲሁ በተመራማሪ ፈታሽነት ማብጠርጠር አማራጭ የለውም። ዋናው ቁም ነገሩ ግን ለኩራትም ሆነ ለስጋት ያሉንን ምክንያቶች በመደርደር ብቻ ሳይሆን ከዚህ የስጋት ምንጮቻችን ተነስተን መፍትሔ መፈላለጉ የግድ ይላል። አነሳሳችን የስጋቱ ቀስት አቅጣጫ በውል ከተለየ በኋላ አስፈላጊውን

መመከቻ ስልት በቦታው ማስቀመጡ አይገድም የሚለውን መሰረተ ግንዛቤ አፅንኦት ለመስጠት ነው።

በስጋቱ ረገድ እንዲሁ በሀገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራው ስደት በድብልቅልቅ ስሜቶች የሚዋዥቁ ኢትዮጵያውን ወገኖች ቁጥር ከፍ እያለ መምጣቱን ነው ልብ የምንለው። በስጋት የሚዋጡ። እንደገናም የሚኩራሩ። የሃገራቸው የወደፊት እጣ ፋንታ ጭልም ጭልምም የሚልባቸው። መልሰው በሃገራቸው በሚታያቸው የዘመናዊ የእድገት ፍንጮች ተበረታተው ብሩህ ተስፋ የሚሰንቁ። ሁላችንም ከእነዚህ ዓይነቱ ስሜቶች ነፃ አይደለንም። ልንሆንም አንችልም። የስጋት፤ የቁጭት የተሰፋ ቅልቅል ስሜቶች ይወሩናል። እነዚሁ መብከንከኖች፤ የውርደትና የብሩህ ተስፋ ስንቅ ስሜቶች መግለጫ (74-75)

እንደ መጽሐፉ አንድምታ የስጋት ምንጭ ከሆኑ ነገሮች ዋነኛው የአብሮ አኗኗሪ ፎርሙላውን (ቀመሩን) ገና አለማግኘታችን ነው። በመጽሐፉ ተገፋፍቶ ያሰበ ሰው ርቆ ሊሄድ ይችላል። አብረን ነን እንጂ አብረን አይደለንም። ራሳችንን በአንድ ሰፍራ አንድ ላይ ተሰብስበን አገኘነው እንጂ አንድ አይደለንም። የሆነ ነገር (ኃይል) ሰብስቦ አንድ ቤት ውስጥ አጉሮናል። እዚያች ቤት ውስጥ ተለያይተንም አንድ ሆነንም መኖር አቅቶናል። ተሸናንፈን እናንተ ዉጡልንና እንኑርበት ማለትም አልቻልንም። ወደዳችሁም ጠላችሁም አንድ ላይ ሁኑ የሚለው መጨፈልቅም አለሆነልንም። ተነጣጥለን እንሞክረው ማለቱም አላዋጣንም። ያለን ምርጫ አስማምቶ አብሮ የሚያኖረንን ቀመር መሻት ነው። ካለበለዚያ ያቺ ቤት መፍረሷ ነው። መጽሐፉማ እንደሚለው ይህ መጋባትና መዋለድ ሁሉ የማይሽረው በመፈቃቀርና በመተሳሰብ የሚለው የአንገት በላይ ሸወዳ የማይሸነግለው ስጋታችን ነው።

ጸሐፊው ከርስትናና እስልምናን ጠቅሰው "ለዘመናት ጎን ለጎን አብሮ በሰላም ኖረዋል መባሉ የሁለቱ ሃይማኖቶች ግንኙነት አልጋ በአልጋ ነበር ማለት ግን አይደለም።" ብለዋል። ግንኙነቱ የሻከረባቸው የታሪክ ምዕራፎች እንደነበሩ በማስታወስ የዛሬ 543 ሁለተኛው የነበረውን የኢማም አሕመድ ኢብን እብራሂም አል-ቃዚ (1529- 1543) ወይም የአሕመድ የግራኝ "እስልሙ" እና የዛሬ 140 ዓመታት ገደማ የተከሰተውን የአፄ ዮሃንስ (1879-1889) "ክስትኑ" ዘመቻዎች በግንባር ቀድምትነት ጠቅሰዋል። ሁለቱም ዘመቻዎች ኢትዮጵያውያኑን በሃይማኖት አንድ-ወጥ የማድረግ ዓላማ ነበራቸው። ሁሉቱም የእምነት ልዩነትን አንድ በማድረግ መፍትሔ የመሻት ግጭቶች ነበሩ። የአብሮነትን ችግር ባንድ አዋሃጅ እምነት እንዲተካ በማድረግ እልባት የመስጠት ሙከራ አድርገዋል ። ግን ሁለቱም ሙከራዎች አልተሳኩም። "ያም ሆኖ ግን አሁንም ቢሆን ለሁለቱም እምነቶች ጎን ለጎን አብሮ አኗኗሪ ቀመርም ተገኘ ማለት እንዳልሆነም እሙን ነው።" ብለዋል ጸሐፊው። ተሸናንፈው መኖሩም ልዩነቶቻቸውን ያለ "ስጋት" አዝለው መኖሩም ገና አልሆነላቸውም። እንግዲህ አብሮ መኖሩ

ቢያኮራ ደበቅ ተደርጎ የተተሸገው "ስጋትም" አልተወገደም። አፍርጠው አይነጋገሩት ነገር.... እሱን መነካካት አያስፈልግም!.. ይህን የተረዱትም ጸሐፊ እንዲህ በማለት ጽፈዋል፤

"የሶይሾሎጂ አጥኚዎች በተለያዩ የሕብረሰቡ ክፍፍሎች መካከል በግልፅ ሊወያዩበት የማይችሉ ርእሳነ- ጉዳዮች አሉ ይሉናል። ለውይይት የማይመቹ። የሚያሸማቅቁ ርእሶች። በእኔ እምነት፤ የሁለቱ ሃይማኖቶች ግንኙኘነት ጉዳይም በእዚሁ አይነሴ ፍረጃ ውስጥ የሚካተት ርእስ ጉዳይ ነው፤ በኢትዮጵያችን። ይህንን እውነታ መካካዱ አሁንም ይህንኑ ለግልፅ ወይይት አለመመቻቸቱን ይበልጥ ያረጋግጣል። ዛሬ በዚህ ላይ ተማምኖ በግልፅ መነጋገሩ አማራጭ እንደሌለው መቀበል ነው አዋጪው። በኢትዮጵያውን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖቹ መካከል ለንግግር ከማይመቹ ርእሰ ጉዳዮቹ አንደኛው ይኸው ነው ማለት ይቻላል።" በማለት "መሰበር ያለበት ዝምታ ነው። ክልከላ ከሆነም መነሳት ያለበት ክልከላ ነው።" ሲሉ ጽፈዋል።

ጸሐፊው ይህን ይህን ማንሳታቸውን ለማሳየት ነው እዚህ ቀነጫጭበን ያነሳነው። መጽሐፋቸውማ በብዙ አስረጂዎችና ትንተናዎች እንጂ እንዲህ በቁንጽል አላነሳቸውም። በሃይማኖት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን እንዲያውም ከዚያ በበዛው መልኩ የብሔረሰቦችና መሰል የማህበራዊ ማንነት ጥያቄዎችን አንስቷል። እሱን ጥያቄ አንገበው የተነሱትን የብሄር ድርጅቶችም ሆነ እንደዚያ ያሉ የብሔር ጥያቄዎች ጨርሶ መነሳት የለባቸውም የሚሉትንም ሁሉ እያነሳ ፈትሿቸዋል። ሁሉም ማለት እንኳ የማያስማማ ቢሆን አብዛኞቹ ግን በኃይል ተጨፍልቀን ተቀላቀልን እንጂ እኛማ ራሳችንን ነበርን ባዮች መሆናቸውን ጽፏል። ልክም ትክክልም ናቸው ብሎ ተስማምቶ ሲያበቃ ታዲያ ምን ይደረግ ብሎ መልሶ ደግሞ ይጠይቃቸዋል። ብሔርተኞቹን ይህን ጥያቄ በማንሳት እስከዛሬ የሄዳችሁበት መንገድ ወዴት ወሰዷችኋል? የትስ አድርሷችኋል እያለ ይጠይቃቸዋል።

"ዋናው ፍሬ ነገሩ ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ አመሰራረት ጉልበት የታከለበት አካሄድ ነበረ። እንደማንኛውም ይህንን ዓይነቱ ትልም። በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ያለ ጉልበትና ጦርነት የተጠናቀቀ የመንግሥት ግንባታ ነበረ ማለት አያስኬድም። በቀድሞ ታሪክ የምናውቃቸው ሰፋፊዎቹ አፄ ግዛቶችም ሆኑ ዘመናውያኑ ብሔረ-መንግሥታት የተወለዱት በጦርነት አማካኝነት ነው። መንግሥት ጦርነት ይፈጥራል ፤ ጦርነትም በተራው መንግሥትን ይፈጥራል መባሉ የተወሰነ እውነተኛነት ያለው አባባል ነው። ሁለቱም ተደጋጋፊ ናቸው። ዘመናዊቷ ኢትዮጵያም እንደ ሌሎቹ መንግሥታት ሁሉ በጦርነት ነው የተወለደችው። ....በአፍሪካም በጥቅል በሃገራችንም በተለይ የታየው አተገባበርም ከእዚሁ ያፈነገጠ ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ለምሳሌ እንደ ኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ ) አይነቶቹን አፄዎቹ ወይም ኢምፓዬሮች በውስጣቸው የተለያዩ ሕዝቦች በግዛቱ ውስጥ የተካተቱት ያለ ውዴታቸው

በግዴታ የተያዙ ናቸውና መፍረስ ይኖርባቸዋል ከሚሉት ኢምፓዬር ይፍረስ ባዮች ጋር እንደሚመሳሰሉ ጽፈዋል። (223-224)
የአቶ ዩሱፍ መጽሐፍ እንደ መማሪያ ማመሳከሪያ መጻሕፍት ሆኖ ሊያገለግል የሚችልም ነው። ለብቻቸው እየተነጠሉ የሚነበቡ ከሌሎች ተጣምረው ፍሬ የሚሰጡ ብዙ ትምህርታዊ ነገሮች አሉበት። ለምሳሌ ሐይማኖትና መንግሥትን ጣልቃ ስለገቡባቸውና ስለተለያዩባቸው አገሮች ግንዛቤ ይኖር ዘንድ የሚከተለውን ጽፈዋል።

በዓለም ሙስሊም አማኝ ከሚበዛባቸው ሃገራት ወደ ስድስቱ ሙስሊማዊ የሚሰኝ መለያ አላቸው ሲጠሩ። ኢራን፣ፓኪስታን፣ አፍጋኒስታን ሞሪታኒያ፣ የመንና ሳዑዲ ዓረቢያ ናቸው። የመጀመሪያው ሦስቱ ዓረባዊ ያልሆኑ ሙስሊም ሃገሮች ሲሆኑ በኋላ ላይ የተጠቀሱት ደግሞ ዓረባውያን ሃገራት ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የመንግሥቱ ሃይማኖት ሙስሊም ነው የምትለዋን ሓሐረግ ያስቀምጣሉ። በዚሁ ተራ ውስጥ 18 ሙስሊም፣ በአብዛኛው ዓረብ ሃገሮች ተካተዋል። አንዳንድ ሃገራት ምንም እንኳን ግልፅ እስታተስቲካዊ አሓሐዝ ደረጃ ብዛት ያለው ሕዝብ የሙስልም መሆኑ ቢረጋገጥም ቅሉ ለምሳሌ ሴናጋል፣ ኒጀር፣ ማሊ የመሳሰሉ የምዕራብ አፍሪካ የቀድሞ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛቶች፣ ሰኩላር ናቸው በሕገ መንግሥቶቻቸው መሠረት። እስካሁን የምትለዋን ሓሐረግ መጨመሩ ሳያዋጣ አይቀርም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚያን ክፍለ አህጉር የሚንቀሳቀሱት እምነት-ጠበቅ ሃይሎችኃይሎች ወደ ሥልጣን ኮርቻ መምጣት ከተሳካላቸው ምን እንደሚወስኑ ከወዲሁ መተንበይ አስቸጋሪ ሆኖዋልና። በዚያን መጠን በአሓዝ ሲሰላ በጣም ከፍተኛ የሕዝቦቻቸው እምነት እስልምና ሆኖ እስካሁን ሰኩላር መንግሥት ባለቤት የሆኑት የመካከለኛ ኤሺያ ሃገሮች እስከ 1991 ድረስ የቀድሞ የሶቭዬት ሕብረት አካል የነበሩት እነ ታጂክስታን፣ አዘርቢጃን፣ ቱርኩማኒስታን፣ ኡዝቤኪስታንና ካዛኪስታን ጭምር ሃይማኖታዊ ብሔራዊ ማንነት ገላጭና አፍታቺ አንቀፅ በሕገ መንግሥታቸው አልተቀመጠም። እስካሁን የምትለዋን ሐረግ መጨመር አይከፋም፣ ለደጉም፣ ለክፉም። በዓለም ከሁሉም በላይ ሙስሊማዊ ሕዝብ ብዛት የተመዘገበባት ኢንዶኔዢያ ከ210 ሚልዮን ሕዝብ፣ 86% ሙስሊም ነው። ስለ መንግሥቱ እምነታዊ ማንነት ሕገ መንግሥቱ ምንም አይገልፅም። በሌላ አባባል ሰኩላር ናት። ማንም ዜጋም ሆነ የሌላ ሃገር ነዋሪ ያሻውን እምነት፣ ፍልስፍና የመከተል መብቱ የተጠበቀባት ሃገር መሆኗን ያመለክታል።
በእስታቲስትክስ መሠረት ከሕዝቧ 99% ሙስሊም የሆነው ቱርክም ሰኩላር መንግሥት ነው ያላት። በሌላ ቦታ እንደተመለከትነው ከሁሉም ኤውሮፓ ሃገራት ቀደም ብላ ቤተ ክርስቲያንን ከመንግሥት መለያየት "ሀ" ተብሎ  የተጀመረባት ፈረንሣይ እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፤ የሰሜን አፍሪካ ፈላሽ-ዓረብ ዝሪያዎች፣ ብሔራዊ-ክርስትያክርስቲያናዊ ማንነቷ ላይ ደቀኑብኝ የሚትለዋን ፈተናና ተግዳሮት ብዙዎች ዜጎቿን ማሳሰቡን ልብ ብለናል።

በሌላ በኩል፤ የሃገሮቻችን ሕግጋተ መንግሥት ቁራአንና ቶራ ነው ብሎ ስለሚያምኑ ሠዑዲሳዑዲ ዓረቢያና እስራኤል ተጨማሪ በሰው ልጅ የተደነገጉ ሕግጋተ-መንግሥት አያስፈልጉንም ስለሚሉ የተፃፈ ዓለማዊ ሕግጋተ-መንግሥት ያላአፀደቁ ከዓለም ብቸኛ ሁለት ሃገራት ናቸው ማለት ያስደፍራል። የሚያስገርመው ግን ሠዑዲሳዑዲ ዓረቢያም ሆነች እስራኤል በስማቸው ሙስሊም ወይም ዩሁዲ የሚል የማዕረግ ማንጠልጠያ ስያሜ የላቸውም። ቁም ነገሩ፤ እነዚህ ሁለቱ ሃገራት ይፋ የሆነ ብሔራዊ -ሃይማኖታዊ ማንነት ግን ቀርፀዋል። ምክንያቱም የሚመሩት አምላክ ደነገገልኝ በሚሉት ሕግ ነውና። (403-409)

እንደ ዘላቂ መፍትሔው የአብሮ አኗኗሪ ቀመሮች ይፈለጋሉ። ይገኛሉም። ለዚህ አለመግባባት ሥልጣንን ባልተማከለ አደረጃጀት መዘርጋት አንዱ ፍቱን ቀመር (ፎርሙላ) ነው። ያሉት አቶ ዩሱፍ ሌሎች ትላልቅና በርካታ ጽንሀሳቦችንና ነገር ጉዳዮችን አንስተዋል። ተከታዩን በሚቀጥለው የዘኢትዮጵያ ጋዜጣ እትማችን ይዘን እንቀርባለን።